# ወደ ዕውቀት መግቢያ በር

የማህበረሰብ እና የግለሰብ ነፃነት፣ ብልጽግናና ዕድገት የሰው ልጆች መሠረታዊ እሴቶች ናቸው። እነዚህ እሴቶች ገቢራዊ ሊሆኑ የሚችሉት ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸውን ለመጠቀምና በህብረተሰቡ ውስጥ የነቃ ተሳትፎ ለማድረግ በሚችሉ በቂ መረጃ በታጠቁ ዜጎች ችሎታ ብቻ ነው። ገንቢ ተሳትፎና የዲሞክራሲያዊ ዕድገት ደግሞ ከበቂ ትምህርትና እንዲሁም ከነፃና ያልተገደበ የዕውቀት፣ የሃሳብ፣ የባሕልና የመረጃ ነፃነት ጋር በእጅጉ የተቆራኙ ናቸው።

የዕውቀት መግቢያ በር የሆኑ የሕዝብ ቤተ-መፃሕፍት ለግለሰብና ማህበራዊ ቡድኖች ዕድሜ ለማይገድበው ትምህርት፣ በነፃነት ውሳኔ የመስጠት ችሎታ ለማግኘትና ለባሕላዊ ዕድገት እጅግ አስፈላጊ ናቸው። ይህ ማኒፌስቶ የሕዝብ ቤተ-መፃሕፍት ለትምህርት፣ ለባሕልና ለመረጃ ህያው ሃይል መሆናቸውንና ሰላምንና የሕሊና ደህንነትን በወንዶችና በሴቶች ላይ ለማስረጽ እጅግ አስፈላጊ አካል መሆናቸውን ዩኔስኮ ያለውን እምነት ያረጋግጣል።

ስለዚህም ዩኔስኮ ብሔራዊና ክልላዊ መንግሥታት የሕዝብ ቤተ-መፃሕፍትን በመክፈትና በጥራት በማሳደግ በኩል የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበረታታል።

## የሕዝብ ቤተ-መፃሕፍት

የሕዝብ ቤተ-መፃሕፍት ማናቸውም ዓይነት ዕውቀትና መረጃ ለተጠቃሚዎች ዝግጁ ሆኖ የሚገኝባቸው የአካባቢ የመረጃ ማዕከል ናቸው። የሕዝብ ቤተ-መፃሕፍት አገልግሎቶች የዕድሜ፣ የዘር፣ የፆታ፣ የሃይማኖት፣ የብሔር፣ የቋንቋ ወይም የማህበረሰባዊ ደረጃን የተመረኮዘ ልዩነት ሳያደርጉ ሁሉንም በእኩልነት ክፍት ሆነው የሚያገለግሉ ናቸው። በማናቸውም ምክንያት በመደበኛ አገልግሎቶችና መሣሪያዎች መጠቀም ለማይችሉ ለምሳሌ አነስተኛ ቁጥር ላላቸው ቋንቋ ተናጋሪዎች፣ ለአካለ ስንኩላን ወይም በሆስፒታል ወይም በእስር ቤት ለሚገኙ ተጠቃሚዎች ሁሉ ልዩ አገልግሎትና መጠቀሚያዎችን ማቅረብ ይገባል።

በሁሉም የዕድሜ ደረጃ የሚገኙ ተጠቃሚዎች እንደፍላጐታቸው የሚገለገሉባቸውን ተገቢ መጠቀሚያዎች ሊያገኙ ይገባል። የቤተ-መፃሕፍቱ ስብስቦችና አገልግሎቶች ሁሉንም ዓይነት የሚዲያና የዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲሁም ባሕላዊ መጠቀሚያዎችን

ማጠቃለል ይኖርባቸዋል። ከአካባቢው ፍላጐትና ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ከፍተኛ ጥራትና ለህብረተሰቡ አስፈላጊ መሆናቸው መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው። ቤተ-መፃሕፍቱ ውስጥ የሚገኙ መጠቀሚያዎች ወቅታዊ ዝንባሌዎችንና የሕብረተሰቡን ዕድገት እንዲሁም የሰውን ልጅ የዕድገት ጥረትና የፈጠራ ቅርሶች የሚያንፀባርቁ መሆን ይኖርባቸዋል።

የቤተ-መፃሕፍቱ ስብስቦችና አገልግሎቶች ከማናቸውም ዓይነት የርዕዮተ ዓለም፣ የፖለቲካ ወይም የሃይማኖት ቁጥጥር ወይም የንግድ ግፊት ነፃ መሆን አለባቸው።

## የሕዝብ ቤተ-መፃሕፍት ዋነኛ ተልዕኮ

ከመረጃ፣ መሃይምነትን ከማጥፋት፣ ከትምህርትና ከባሕል ጋር የተያያዙ የሚከተሉት ቁልፍ ተግባራት የሕዝብ ቤተ-መፃሕፍት አገልግሎት ማዕከላዊ ነጥብ ናቸው።

1. ሕፃናት ከታችኛው የዕድሜ ደረጃ ጀምሮ የንባብ ልምድ እንዲኖራቸው ማድረግና ይህንኑም ልምድ ማጠናከር፤
2. በየትኛውም ደረጃ የሚገኘን ግላዊና በራስ ጥረት የሚደረግን ትምህርትና እንዲሁም መደበኛ ትምህርትን መደገፍ፤
3. በግል ለሚደረጉ የፈጠራ ጥረቶች ተገቢ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
4. በሕፃናትና በወጣቶች የሚደረጉ ጥልቅ የአስተሳሰብና የፈጠራ ጥረቶችን ማበረታታት፤
5. ባሕላዊ ቅርሶች እንዲታወቁና እንዲጠበቁ መደገፍና የሥነ-ጥበብና የሳይንስ ፈጠራና ግኝቶችን ማበረታታት፤
6. ባሕላዊ ማንነት የሚገለጽባቸው ሁሉም የሥነ-ጥበብ ሥራዎች ለሕዝብ ክፍት የሚሆኑበትን ሁኔታ ማዘጋጀት፤
7. የባህል ልዩነትን ውበት መደገፍና በተለያዩ ባሕሎች መካከል ገንቢ ውይይት እንዲደረግ መጣር፤
8. ባሕላዊ ሥነ-ቃል እንዲያድግ መደገፍ፤
9. ማህበረሰባዊ መረጃዎች ለሁሉም ዜጐች የሚዳረሱበትን መንገድ ማመቻቸት፤
10. ለአካባቢያዊ ድርጅቶች፣ ማህበሮችና ዝንባሌን ተመርኩዘው ለሚደራጁ ማናቸውም ቡድኖች በቂ የመረጃ አገልግሎት ማቅረብ፤
11. የመረጃ እና የኮምፒውተር እውቀት እንዲያድግ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
12. በማናቸውም የዕድሜ ደረጃ ወስጥ የሚገኙ ዜጐችን ከመሃይምነት ለማላቀቅ የሚደረጉ ጥረቶችን መደገፍና በጥረቱ ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እነዚህ ጥረቶች እንዲጀመሩ ማበረታታት።

## የገቢ ምንጭ፣ ሕጐች እና የግንኙነት ሰንሰለቶች

በመርህ ደረጃ የሕዝብ ቤተ-መፃሕፍት ከአገልግሎት ክፍያ ነፃ መሆን ይኖርባቸዋል:: የሕዝብ ቤተ-መፃሕፍት የአካባቢያዊና የብሔራዊ ባለሥልጣኖች ሃላፊነቶች ናቸው:: የሕዝብ ቤተ-መፃሕፍት ለእነርሱ ተብሎ በወጣ ሕግ መደገፍ የሚኖርባቸው ሲሆን ወጪያቸውም በብሔራዊና አካባቢያዊ የመንግሥት አካላት መሸፈን ይኖርበታል:: የባሕል፣ የመረጃ አቅርቦት፣ መሃይምነትን የማጥፋትና የትምህርት የረጅም ጊዜ እቅድ በሚነደፍበት ወቅት የሕዝብ ቤተ-መፃሕፍት እጅግ አስፈላጊ አካል ተደርገው በእቅዱ ውስጥ እንዲካተቱ ያስፈልጋል::

አገር አቀፍ የቤተ-መፃሕፍት ቅንጅትና ትብብር እንዲኖር ለማድረግ ሕጐችና የረጅም ጊዜ እቅዶች የጋራ ስምምነት የተደረሰባቸው የአገልግሎት አሰጣጥ መመዘኛዎችን መሠረት ያደረገ ብሔራዊ የቤተ-መፃሕፍት ጥምረትን እንዲረዱ ሆነው ሊቀረፁ ይገባል::

በሕዝብ ቤተ-መፃሕፍት መካከል የሚኖረው ጥምረት ከብሔራዊ፣ ክልላዊ፣ ከምርምርና ከልዩ ቤተ-መፃሕፍት እንዲሁም ከትምህርት ቤቶች፣ ከኮሌጆችና ከዩኒቨርሲቲዎች ቤተ-መፃሕፍት ጋር ተቀናጅቶ መታቀድ ይኖርበታል::

## ተግባራዊ እንቅስቃሴና አመራር

በአካባቢው ሕብረተሰብ ፍላጐት ላይ የተመሰረቱ አላማዎችን፣ ቀዳሚ ሁኔታዎችና አገልግሎቶችን የሚያብራራ ግልጽ የሆነ ፖሊሲ መዘጋጀት አለበት:: የሕዝብ ቤተ-መፃሕፍት እጅግ ውጤታማ እንዲሆኑ ተደርጐ መደራጀት የሚኖርባቸው ሲሆን ፕሮፌሽናል የአሰራር መመዘኛዎችንም ያሟሉ ሊሆኑ ይገባል::

አስፈላጊ ከሆኑ አካሎች ማለትም በተጠቃሚነት ከተደራጁ ቡድኖችና እንዲሁም በአካባቢ፣ በክልልና በብሔራዊ እንዲሁም በአለም አቀፍ ደረጃ ከሚገኙ ሌሎች የሙያው ክፍሎች ጋር የሚኖረው ትብብር መረጋገጥ አለበት::

የቤተ-መፃሕፍቱ አገልግሎቶች ለሁሉም የሕብረተሰቡ አባሎች ክፍት ሆነው በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ ሆነው መደራጀት አለባቸው:: ይህን ለማድረግም በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጀ የቤተ-መፃሕፍት ህንፃ፣ ጥሩ የንባብና የጥናት አቅርቦትና መሣሪያዎች፣ በተጨማሪም አግባብነት ያለው ቴክኖሎጂና ለተጠቃሚዎች አመቺ የሆነ ክፍት የአገልግሎት ሰዓት ማደራጀት ያስፈልጋል:: ይህም ወደ ቤተ-መፃሕፍት መምጣት ለማይችሉ ሁሉ አለበት ድረስ በመሄድ አገልግሎት መስጠትን ያካትታል::

የቤተ-መፃሕፍቱ አገልግሎቶች በገጠርና በከተማ ከሚገኙ የሕብረተሰቡ ክፍሎች የተለያዩ ፍላጐቶች ጋር እንዲጣጣሙ ተደርገው ሊዘጋጁ ይገባል::

አንድ የቤተ-መፃሕፍት ሠራተኛ ተጠቃሚዎችንና ለአገልግሎት የተዘጋጁ የዕውቀት ክምችቶችን የሚያገናኝ ነው:: ስለዚህም በቂና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት ይቻል ዘንድ የቤተ-መፃሕፍት ሠራተኛው በሙያው ላይ የጠለቀ እውቀት በሚያስገኙና እንዲሁም በተከታታይ የትምህርት መስኮች እንዲሳተፍ ማድረግ የማይታለፍ አስፈላጊ ጉዳይ ነው::

ተጠቃሚዎች በቤተ-መፃሕፍቱ ክምችቶች በአግባቡ እንዲጠቀሙ ለማድረግ በሕብረተሰቡ ውስጥ በቂ ቅስቀሳ ማድረግና ተጠቃሚዎችን በትምህርታዊ ፕሮግራሞች ማሳተፍ ያስፈልጋል::